# በወንዞቻችን የውሃ መበከልን ለመቀነስ፣ ለዝናብ አትክልት ስፍራ ተመላሽ ማግኘት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

በዲሲ ውስጥ ነዋሪዎች በቤታቸው የዝናብ አትክልት ስፍራዎችን በመስራት የውሃ ብክለትን ለመቀነስ ከረዱ፣ ተመላሽ ሊያገኙ ይችላሉ። የዝናብ አትክልት ስፍራዎች የዝናብ ውሃን በማጠራቀም ብክለትን ያጣራሉ። እኛ—የዲሲ መንግስት—እስከ **$2,200 የማጣሪያ አካባቢበ $3 ስኩዌር ጫማ የአንድ ጊዜ ተመላሽ እናቀርባለን** እንዲሁም የዝናብ አትክልት ስፍራዎን ዋጋ አይበልጥም።

ይህ ፕሮግራም RiverSmart Rebates ሲባል የቀረበውም በኢነርጂ እና አካባቢ ዲፓርትመንት ከ Alliance for the Chesapeake Bay (ወይም በአጭሩ Alliance ይባላል) ከሚባል ለትርፍ ከማይሰራ ድርጅት ጋር በመተባበር ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ።

በዲሲ ውስጥ የመኖሪያ ወይም የንግድ ህንጻ ካለዎት ወይም ከተከራዩ፣ ብቁ ነዎት። የሚያመለክቱበት ንብረት ዲሲ ውስጥ እስከሆነ ድረስ እና  የአትክልት ስፍራውን አንድ ሰው እንዲንከባከበው ከመረጡ፣ ለማመልከት ዲሲ ውስጥ መኖር አይጠበቅብዎትም።

## ያመልክቱ።

1. ለእርስዎ የዝናብ አትክልት ስፍራ ምርጡን ቦታ በመለየት ይጀምሩ። በእኛ የዝናብ አትክልት ስፍራ መመሪያ ያለውን ይከተሉ። ከእርስዎ መሰረት እና ከንብረትዎ መስመሮች የዝናብ አትክልት ስፍራዎ ምን ያህል ሩቅ እንደሆነ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልግዎታል። ስለ ዝናብ አትክልት ስፍራው ቦታ ማንኛውም ጥያቄዎች ካለዎት፣ ለትርፍ በማይሰራው ድርጅት Jordan Gochenaur (jgochenaur@allianceforthebay.org) በ Alliance for the Chesapeake Bay (ወይም በአጭሩ the Alliance) እርዳታ ለማግኘት ያነጋግሩ!
2. የውሃ ፍሳሾች ከአፈሩ በምን ያህል ፍጥነት እንደሚፈስሱ ለማየት የመረጡትን ስፍራ ይመርምሩ። ይህ የ percolation ምርመራ (ወይም በአጭሩ perc ምርመራ) ይባላል። የ perc ምርመራ ወርክሺትን ያጠናቅቁ እንዲሁም በማመልከቻዎ ውስጥ ለማካተት ይዘውት ይቆዩ።
3. የተተከለበት ቦታን ያለ አትክልት ስፍራው ፎቶዎችን ያንሱ እንዲሁም በማመልከቻዎ ውስጥ ለማካተት በዛው ላይ ይያዟቸው።
4. የዝናብ አትክልት ስፍራዎን ለመስራት፣ የመሬት ገጽ ባለሙያ ይምረጡ። የእርስዎ የዝናብ አትክልት ስፍራ በትክክል እንደሚሰራ ለማረጋገጥ እና ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ፣ የዝናብ አትክልት ስፍራ በተሳካ ሁኔታ በመስራት ልምድ ያለውን የመሬት ገጽታ ባለሙያ እንዲመርጡ እንመክርዎታለን። በ መሬት ገጽ ባለሙያዎች ዝርዝር ህብረት ውስጥ ባለውና የተመላሽ ፕሮግራምን በደንብ የሚያውቀውን Jordan Gochenaur

(jgochenaur@allianceforthebay.org) ያግኙ። የዝናብ አትክልት ስፍራ እራስዎ የሚሰሩት ከሆነ፣ የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ይወቁ።

5. የንድፍ ስኬች (በእኛ የዝናብ አትክልት ስፍራ መመሪያ ውስጥ ያለው ምሳሌ) እና በእያንዳንዱ ንጥል ላይ ያለ በጀት ያዘጋጁ። በዝናብ አትክልት ስፍራው መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ንድፍዎ ማሟላት አለበት እንዲሁም ለበጀትዎ በማመልከቻው ጥቅል ውስጥ ያለውን የናሙና ንጥል የመክፈያ ደረሰኝ ወርክሺት መጠቀም ይችላሉ። ከመሬት ገጽ ባለሙያው ጋር የሚሰሩ ከሆነ፣ ይህንን ደረጃ ለማጠናቀቅ ከእርስዎ ጋር መስራት አለባቸው እና የንድፍና የክፍያ ደረሰኝ ክፍሎችን ከማጠናቀቅ ይልቅ፣ የእነርሱን ፕሮፖዛል ወደ ማመልከቻው ማያያዝ ይችላሉ።
6. የማመልከቻውን ቅጽ እና የጥገና ስምምነቱን ያጠናቅቁ። RiverSmart Rewards በሚባለው በእርስዎ DC Water ክፍያዎ ላይ ለቅናሽ ለማመልከት፣ ለእርስዎ በማመልከቻው ጥቅል ውስጥም እንዲሁ በአንድ ጊዜ ቅጽ አካትተናል።
7. የተሞላውን ማመልከቻ፣ የጥገና ስምምነት፣ perc የምርመራ ወርክሺት፣ ንጥል የክፍያ ደረሰኝ እና ከመሰራቱ በፊት ያሉ ፎቶዎችን ያስገቡ። ወደ Jordan Gocheanaur (jgochenaur@allianceforthebay.org)ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ ወይም ወደሚከተለው በፖስታ ይላኩ፡

   Jordan Gochenaur
   Alliance for the Chesapeake Bay
   729 8th Street, Suite 200
   Washington, DC 20003

የዝናብ አትክልት ስፍራዎትን ከመስራትዎ በፊት፣ እኛ ጋር ያለውን የዝናብ አትክልት ስፍራ መመሪያመስፈርቶች በሙሉ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ አመልክተው ተቀባይነት ለማግኘት መጠበቅ አለብዎት። የዝናብ አትክልት ስፍራዎ ከተሰራ እስከ አንድ አመት ውስጥ ማመልከቻዎን ካስገቡ፣ ማመልከቻዎን ከግምት ውስጥ እናስገባዋለን፣ ነገር ግን በእኛ ላይ ያለውን የዝናብ አትክልት ስፍራ መመሪያ መስፈርቶች በሙሉ ካላሟላ፣ ለተመላሽ ብቁ አይደለም ማለት ነው።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

### ካመለከትኩ በኋላ ምን ይሆናል?

1. ከ 2-3 ሳምንታት ውስጥ፣ Alliance for the Chesapeake Bay (ወይም በአጭሩ the Alliance) ማመልከቻዎን ይገመግምና፣ ተቀባይነት ካገኘ ኢሜይል ያደርግልዎታል ወይም ይደውልልዎታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ the Alliance የዝናብ አትክልት ስፍራውን ለመስራት ያቀዱበትን ቦታ ለመመርመር መርሃ ግብር ይይዛል። በ RiverSmart ቤቶች ፕሮግራም በኩል ምርመራ ቀድሞ ካስደረጉ፣ ሌላ ምርመራ አያስፈልግዎትም።
2. ማመልከቻው በ the Alliance ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣ እራስዎ ወይም የመሬት ገጽታ ባለሙያው የዝናብ አትክልት ስፍራውን ያዘጋጁ። እንደ አማራጭ የቀረበ ነው ነገር ግን የሚችሉ ከሆነ፣ ከእርስዎ

የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽ ጋር ለማካተት የዝግጅቱን ሂደት ፎቶዎችን ያንሱ ( ደረጃ #5 ይመልከቱ)።

3. በእኛ [የዝናብ አትክልት ስፍራ መመሪያ] መሰረት የአትክልት ስፍራው ሁሉንም መስፈርቶች እንዳሟላ ለማሳየት፣ የተዘጋጀውን የዝናብ አትክልት ስፍራ ፎቶዎችን ያንሱ። ከፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽዎ ጋር ለማካተት እነዚህን ይያዙ (ደረጃ #5 ይመልከቱ)።
4. [የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽን] ከመጨረሻው የንድፍ እና የዝናብ አትክልት ስፍራ ስራ ወጪ መረጃ ጋር ያጠናቅቁ።
5. የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽዎን እና ከዛ በኋላ ያሉትን ፎቶዎች ለ Jordan Gochenaur በ jgochenaur@allianceforthebay.org ላይ ያስገቡ።
6. የእርስዎን የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ቅጽ ካስገቡ በኋላ ባሉት 2-3 ሳምንታት፣ የዝናብ አትክልት ስፍራውን የሰሩበት ስፍራን የመመርመር መርሃ ግብር ለማስያዝ the Alliance ኢሜይል ያደርግልዎታል ወይም ይደውልልዎታል።
7. የዝናብ አትክልት ስፍራዎን the Alliance ከመረመረና ካጸደቀ በኋላ ባሉት ስድስት ሳምንታት፣ በማመልከቻዎ ላይ ባለው አድራሻ ለተመላሽዎ በፖስታ ቼክ ይልክልዎታል።
8. የእኛን [የጥገና መመሪያ] በመከተል ተክሎችን ማጠጣት፣ አረም ማረም እንዲሁም የውሃ መውረጃ ቱቦ መውጫውን መጥረግን በማካተት የዝናብ አትክልት ስፍራውን ይጠብቁታል እንዲሁም ይንከባከቡታል። በትክክል እየሰራ እንደሆነ ለማረጋገጥ፣ የአትክልት ስፍራዎ መደበኛ የሆነ ትኩረት ይፈልጋል። የዝናብ አትክልት ስፍራዎን እንዴት መጠበቅ እንዳለብዎት ምክር ከፈለጉ፣ ለ the Alliance [ጥያቄ ማስገባት] ይችላሉ።
9. ሁሉም ነገር በትክክል እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ፣ የ DC Government ወይም the Alliance በዘፈቀደ ቤትዎን ሊመርጡት ይችላሉ። የአትክልት ስፍራዎ ለምርመራ ከተመረጠ፣ የምርመራውን መርሃ ግብር ለማስያዝ ኢሜይል እናደርግልዎታለን ወይም እንደውልልዎታለን።

ተቀባይነት ካላገኙ፣ ባመለከቱ በሁለት ሳምንታት ውስጥ እርስዎን ለማሳወቅ ኢሜይል እናደርግልዎታለን ወይም እንደውልልዎታለን። ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎ ቦታ ወይም ንድፍ ላይ ምን ዓይነት ለውጦች ማድረግ እንደሚችሉ እናሳውቅዎታለን። ከዛም ማመልከቻዎን እንደገና እንድንገመግምልዎ የተከለሰ የንድፍ ስኬች፣ የንጥል ክፍያ ደረሰኝ፣ perc ምርመራ ወርክሺት እና/ወይም ከስራው በፊት ያሉ ፎቶዎችን መላክ ሊያስፈልግዎት ይችላል።

**ሁሉም ብቁ አመልካቾች ተመላሹን ያገኛሉ?**

አዎ። በእኛ [የዝናብ አትክልት ስፍራ መመሪያ] ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የእርስዎ የዝናብ አትክልት ስፍራ እስካሟላ ድረስ፣ ተመላሽ ያገኛሉ።

**ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**

ለፕሮጀክትዎ ፈቃዶች ሊያስፈልግዎ ይችላል። ለፈቃድ መስፈርቶችና ፈቃድ ለማግኘት እንዴት ማመልከት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት፣ [በሸማች እና ቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ የቤት ባለቤቶች ማዕከልን] ይጎብኙ።

**ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?**
መጀመሪያ፣ ከገጹ ታች በታ ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካለዎት፣ Jordan Gochenaur በ the Alliance for the Chesapeake Bay ላይ በስልክ ቁጥር (202) 553-6483 ያነጋግሩ። ወይም ለ Jordan በ jgochenaur@allianceforthebay.org ላይ በርዕስ መስመር "Rain Garden Rebate Question" ብለው ኢሜይል መላክ ይችላሉ። ስራው ከመከናወኑ በፊት ያሉ ፎቶዎችን ያካትቱ።

ስለፕሮግራሙ በዲሲ መንግስት ውስጥ ያለን አንድ ሰው ለማነጋገር ከፈለጉ፣ የእኛን RiverSmart ቤቶች ቡድንን በ (202) 535-2252 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ሰዓት ውስጥ ማግኘት ይችላሉ ወይም ወደ እኛ በriversmarthomes@dc.gov በርዕስ መስመር "Rain Garden Rebate Question" ብለው ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

**በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
ቤትዎን ለአካባቢ ተስማሚ የሚያደርጉ እርስዎን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ተመላሼ የሚሰላው እንዴት ነው?**

ተመላሹ የሚያጠቃልለው የዝናብ አትክልት ስፍራውን ራሱንና ወደ ዝናብ አትክልት ስፍራው የሚፈስሱ አካባቢዎችን ነው (የጣሪያ ጫፎች፣ የኮንክሪት ጓሮዎች፣ የአስፋልት መንገዶች)። የሚጸዳው አካባቢ ቢያንስ 400 ስኩዌር ጫማ መሆን አለበት። ለምሳሌ፣ ባለ 50 ጫማ የሚሆን የዝናብ አትክልት ስፍራ ቢሰሩ እና ውሃ ከ 450 ስኩዌር ጫማ የጣራ ማፍሰሻዎ ወደ የዝናብ አትክልት ስፍራ እንዲፈስስ ንድፍ ቢያወጡ፣ $1,500 የሚሆን ተመላሽ ($3 x 500 ስኩዌር ጫማ) ማግኘት ይችላሉ።

**የእኔን የዝናብ አትክልት ስፍራ ወይም የጥላ ዛፍ ወይም የዝናብ በርሜልን የመሳሰሉ ሌሎች የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ሳዘጋጅ እርዳታ ላገኝ እችላለሁ?**

ምን አልባት! የእኛ RiverSmart Homes ፕሮግራም ዝቅተኛ ዋጋዎች እና ለዝናብ በርሜሎች፣ ዛፎች፣ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች እንዲሁም ቤይስኬፒንግ የማዘጋጀት እርዳታዎችን ያቀርባል። ነጠላ የቤተሰብ ቤት (ወይም አራት ወይም አምስት ክፍሎች ያሉት ህንጻ) ካለዎት፣ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለ 50 ስኩዌር ጫማ የዝናብ አትክልት ስፍራ (በእያንዳንዱ ንብረት እስከ ሁለት) $100 ይከፍላሉ እንዲሁም ዝርጋታውን ጨምሮ እኛ የቀረውን እንሸፍናለን። በRiverSmart Homes በኩል ከ 75 ስኩዌር ጫማ በላይ የሆኑ የዝናብ አትክልት ስፍራዎች ከተፈቀደልዎ፣ የቀረውን ወጪ ለመሸፈን ለተመላሽ ክፍያ ሊያመለክቱ ይችላሉ።

የሚከተለውን ከመረጡ፣ RiverSmart Homes ከRiverSmart Homes ይልቅ ለእርስዎ የተሻለ ተስማሚ ሊሆን ይችላል፡

- በእኛ የዝናብ አትክልት ቦታ መመሪያ ላይ ያሉትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ፣ የዝናብ አትክልት ስፍራውን እራስዎ ይንደፉ
- ለመሬት ገጽታ ባለሙያው ለመመደብ ረጅም የመጠበቅ ጊዜያትን ያስቀሩ
- የራስዎን የመሬት አቀማመጥ ይምረጡ ወይም እራስዎ ያድርጉ

## የጥላ ዛፍ እና የዝናብ በርሜልን የመሳሰሉ ሌሎች የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ተመላሽ ለማድረግ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በራስዎ ወይም እርስዎ በመረጡት ገንቢ ባለሙያ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶችን ሲገነቡ፣ ከእኛ - የዲሲ መንግስት ተመላሽ መቀበል ይችላሉ። የብቁነት መስፈርት፣ የማመልከቻ ሂደት፣ እንዲሁም የተመላሽ መጠን በፕሮጀክቱ አይነት ላይ በመመስረት ይለያያል እንዲሁም ከመገንባትዎ በፊት መተግበር ሊኖርብዎት ይችላል። ተመላሽ ስለምንሰጥባቸው የሚከተሉት ፕሮጀክቶች የበለጠ መማር ይችላሉ፡

- የዝናብ ውሃን ለመያዝ የሚያስችሉ ተክሎችን እድገት ለመርዳት የሚሆኑ**አረንጓዴ ጣሪያዎች**
- ከተለመደው አስፋልትና የኮንክሪት ገጽ ይልቅ የዝናብ ውሃን ለመያዝና በጊዜያዊነት ለማቆየት የሚያስችሉ **አስተላላፊ ገጽታች**
- በኋላ ላይ የአትክልት ቦታዎን ለማጠጣት ወይም መኪናዎን ለማጠብ የሚሆን የዝናብ ውሃ የሚያጠራቅምና የሚይዙ **የዝናብ በርሜሎች**
- **የጥላ ዛፎች**በአፈሩ ላይ የዝናብ ውሃ ማቆየትን የሚረዱ

## የዝናብ አትክልት ስፍራ በማድረጌ ሌላ የገንዘብ እርዳታ ላገኝ እችላለሁ?

አዎ! ለዚህ ፕሮግራም ሲያመለክቱ፣ በ DC Water ክፍያዎ ላይ RiverSmart Rewards ለሚባለው ቅናሽ ማመልከት እንዲችሉ እንረዳዎታለን። ይህ ቅናሽ እንደ ዝናብ አትክልት ቦታዎች ያሉ የበቁ አረንጓዴ ፕሮጀክቶችን በመጠቀም የውሃ ፍሰትን በንብረታቸው ላይ እንዳይሆን ለሚከላከሉ የንብረት ባለቤቶች ነው።

## እነዚህ አረንጓዴ ፕሮጀክቶች የዲሲ ከተማን እንዴት ሊረዱት ይችላሉ?

እንደ ዝናብ በርሜሎች፣ የዝናብ አትክልት ቦታዎች እንዲሁም የጥላ ዛፎች ያሉ የአረንጓዴ ፕሮጀክቶች ወደ ንብረትዎ እና ወንዞችዎ የሚፈስሰውን የተበከለ የዝናብ ውሃ መጠን ለመቀነስ ይረዳል። ይህ የ Anacostia ወንዝን፣ Potomac ወንዝን እና Rock Creek ከጎጂ ብክለት እንድንጠብቃቸው ይረዳናል።

## ተቀባይነት ሳላገኝ ብቀር ለፕሮግራሙ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?

አዎ። በሁኔታዎ ላይ ያለው ለውጥ ብቁ ያደርገኛል ብለው ካመኑ፣ እንደገና ለተመላሽ ማመልከት ይችላሉ።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*